# በምርጫ መሸነፉን ከወዲሁ ያመነው ተቃዋሚ

ዋቅቶላ ሁንዴ

08/06/14

የዚህ ፅሁፍ መነሻ ነገረ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ሐምሌ 8 ቀን 2006 ዓ.ም በቅጽ 1 ቁጥር 21 እትሟ በነፃ መድረክ አምዱ ያሰፈረችው እያስፔድ ተስፋዬ "በምርጫው መሳተፍ በሕዝብ መቀለድ ነው" በሚል ርዕስ ያስነበበው ፅሁፍ ነው፡፡

የግንቦት ሰባትና የሰማያዊ ፓርቲ ርዕዮተ ዓለማዊ ልሣን በሆነችው ፋክት መጽሔት ላይ ዶክተር በድሉ ዋቅጅራ"…ስለ…ሲባል ምርጫው ይቅር" የሚል ፅሁፍ መፃፋቸውን ተከትሎ አቶ ግርማ ሰይፉና አቶ ታምራት ታረቀኝ ምርጫው መቅረት የለበትም፣ ተቃዋሚው በንቃት መሳተፍ አለበት በሚል ላቀረቡት የሀሳብ ምልልስ እያስፔድ ተስፋዬ አክብሮቱን ገልፆ በቀጣዩ ምርጫ መሳተፍ በሕዝብ መቀለድ መሆኑን ገልጿል፡፡

ፋክት በተለያዩ እትሞቿ ያስነበበቻቸውን የአመፅ የትግል ሥልቶች፣ ሕዝባዊ ንቅናቄዎች፣ የታሰሩት ካልተፈቱ፣ በውጭ ያሉት ወደ አገር ካልተመለሱ፣ ምርጫ ቦርድ ካልፈረሰ…ወዘተ በማተት በምርጫው አንሳተፍም የሚለውን የቀደመ ዝግጅት እያስፔድ እንደ አዲስ ሊነግረን ሞክሯል፡፡

ፋክት መፅሔት በቀጣዩ ምርጫ አለመሳተፍንም ተቃዋሚው ሊያየው ይገባል ስትል በርዕሰ አንቀጽዋ የፃፈችውንም ልብ ይሏል፡፡ ይህ በሆነ በሁለት ሣምንታት ውስጥ የአንድነቱ ፓርቲ ሰብሳቢ ለአንድ ጋዜጣ በሰጡት ቃለ ምልልስ የጠየቅናቸው ሁኔታዎች ካልተሟሉ በምርጫው አለመሳተፋችንንም እንደ አማራጭ እናያለን ብለዋል፡፡

ቅድሙንም ለተዘጋጃችሁበት የአመጽ ጥሪና ቅስቀሳ፣ ሕዝባዊ የተቃውሞ ሠልፍ ንቅናቄ፣ ሥራ ማቆም አድማ፣ ኢኮኖሚያዊ አሻጥርና ደባ፣ ወጣቱን ለተቃውሞ ማነሳሳት፣ በቡድን ማደራጀት፣ የገዢውን ፓርቲ አባላት ዒላማ ማድረግ፣ ከገዢው ፓርቲ ጋር ግንኙነት አላቸው ከሚባሉ የንግድ ድርጅቶች አለመግዛት፣ በማህበራዊ ሕይወት ማግለል ወዘተ…በምርጫው አለመሳተፍ፣ አሁን ደግሞ የምርጫ ካርዱን ሕዝቡ እንዲያቃጥል

ማድረግ በማለት ያላላችሁት፣ ያልለፈፋችሁት መዓት አውርድ ጥሪ የለም፡፡ ሕዝብ ይህንንም ይሰማል፣ ያያል፣ ይታዘባል፣ ፍርድም ውሣኔም ይሰጣል፡፡ ለዚህም አትቸኩሉ፡፡

ምርጫው ገና በመጪው ግንቦት 2007 የሚካሄድ ሆኖ ሳለ እነ እያስፔድ ተስፋዬ ገና ሐምሌ 2006 ላይ ወደ ምርጫ ውድድር አንገባም፣ አንሣተፍም ስትሉ ገና ወደፊት አንድ ዓመት የቀረውን ምርጫ በመፍራት ከወዲሁ ተጭበርብሯል እያላችሁ ነው፡፡ ይህም ከፍ ያለ የፖለቲካ ኪሣራና ውድቀት ላይ መሆናችሁን ያሳያል፡፡

በእርግጠኝነት እናንተ ራሳችሁ ኢ.ሕአዴግ እንደሚያሸንፍ አምናችኋል፡፡ የማንችለው ውድድር ውስጥ ገብተን በውርደት ከምንሸነፍ አሪፍ የሆነ የአራዳ ልጅ ዘዴ ፈጥረን ከወዲሁ ሰሚ የለም እንጂ ሕዝቡን ለአመጽ ቀስቅሰን በማስነሳት አገሪቷን በሁከት እናምሳት እያላችሁ ነው፡፡ ይኼ ነው ዋነኛው የውድቀታችሁ ምልክት፡፡

ለሰሚው ግራ ገንፎ በአሬራ እንዲሉ ምርጫው ውስጥ ገብታችሁ ውጤቱን ሳታውቁት ምኑን በመቃወም ነው ተቃውሞ የምትቀሰቅሱት፣ ምርጫ ሳይደረግ ገና ለገና ይጭበረበራል ብለን ስለፈራን ከአሁኑ መጮህ አለብን የሚለውን ምክንያት የእናንተ አምላኮች የሆኑት ምዕራባውያንም አይቀበሉትም፡፡ በምርጫዎች ዓለም አቀፍ ህግና ደንብ መሠረት ተቃውሞ ቢኖር እንኳን የሚጠየቀው የሚነሳው ከምርጫው በኋላ ነው፡፡ እናንተ ግን ረዥም ጊዜ ወስዳችሁ ስትሰሩበት የቆያችሁት አመፅ ለመቀስቀስና ትርምስ እንዲፈጠር ነው፡፡

ከአክራሪና ከአሸባሪ ኃይሎችም ጋር በሕብረት በእርግጠኛነት የቆማችሁ በመሆኑ ለፖለቲካ ሥልጣን ያበቃናል ብላችሁ ያሰባችሁት ብቸኛ መንገድ ሕዝባዊ አመፅ፣ ቂጣ ማነሳሳት፣ ለእለት እንጀራው የሚሮጠው ሕዝብ ሥራውን ትቶ የእናንተን ሠልፍ አድማቂ ሆኖ በየጎዳናው ሲጮህ እንዲውል ነው ፍላጎታችሁ፡፡

ጥቂት ሆናችሁ መጮህ ትችሉ ይሆናል፡፡ ጥሩምባ መንፋትና እሪታ የሕዝብን ሠላም መንሳትና ማወክ በመሆኑ አይፈቀድም፡፡ እናንተ ለአገርና ለወገን በመቆርቆር ስም ለምትፈጥሩት አገርና ሕዝብን የማናጋትና ሠላምን የማደፍረስ ከጀርባው በፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ለሚደገፍ ተልዕኮ ሕዝቡ ሁሉንም ስለሚያውቅ አብሮን ይሰለፋል ብላችሁ ማሰባችሁም ራሱን ችሎ ትልቅ ስህተት ነው፡፡

በ1997 ዓ.ም ያንን ሁሉ ዋጋ ያስከፈላችሁትን ሕዝብ እኮ ነው ዛሬም የትናንቶቹ ሰዎች ስምና ካባችሁን ለውጣችሁ በዚያው አቋም እናንተም ልጆቻችሁም ለእኛ ስትሉ የደም ዋጋ ከፈሉልን፣ ሙቱልን እያላችሁት ያላችሁት፡፡

ትናንት ስለደረሰውም ሁሉ መነሻ ምክንያቱ፤ ለተከተለውም ጥፋትና ውድመት መንስዔዎቹ እናንተው ናችሁ፡፡ ያኔስ ተደራጅታችሁ መሣሪያ ለመንጠቅ፤ ፖሊስ ጣቢያ ለመውረር አልተሞከረም? ቦምብ አልተወረወረም? የፈላ ውኃ በየቤቱ እንዲዘጋጅ ቅንጅቱ አዞ ሴቶች አላፈሉም? የፈላ ውኃ የተደፋበት የለም? ሠላም ለማስከበር መሣሪያ ይዞ የቆመ ፖሊስ ወይንም ወታደር ደብድበንህ መሣሪያህን እንንጠቅህ ሲሉት አቶ እያስፔድ ምላሹ ምን የሚሆን ይመስልዎታል?

ፀጥታ አስከባሪው መሣሪያውን አላስነጥቅም ሲል በግብግቡ ጥይት ይጮኃል፤ ሰው ይወድቃል፤ ባንክ ሰብረን እንዝረፍ ብለው በድንጋይ ውርወራ ሲረባረቡና ባንኩን መስበር ሲጀምሩ መሣሪያ ይዞ ለጥበቃ የቆመው ወታደር መሠረታዊ ኃላፊነቱ ሕይወቱንም ከፍሎ ቢሆን ባንኩን ማዳን ነውና የዚያን ወቅት ጥይት ይጮኃል ሰው ይወድቃል፤ የመንግሥትና የሕዝብ ተቋማትንና ንብረትን በድንጋይ እንደብድብ፤ በእሣት እናጋይ፤ መቼ ነው እድሉ ገጥሞን የሰው ሐብት፣ ሱቅ፣ ወርቅ ቤት ወዘተ...ዘርፌ የምከብረው ብሎ ሲያስብ የቆየ የመንደር ጎረምሣ ስብስብ እናንተ የከፈታችሁትን የጥፋት በር ተከትሎ በሚፈጠረው ሥርዓት አልበኝነት ለዘረፋ ሲሰማራ ያኔ ንብረትና ሐብት ለመጠበቅ የቆመው ፖሊስ ወይንም ወታደር አላዘርፍም ሲል በኃይል እንጠቀም ስትሉ ጥይት ይጮኃል፤ ሰው ይወድቃል፤ እናንተ ለሠላማዊው ሕዝብና ለልጆቹ የደገሳችሁለት የእልቂት ድግስ ብዙ ቢሆንም አይሳካላችሁም፡፡

ቀደም ባሉ ዓመታት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በመጠቀም ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያምና ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ውስጥ ውስጡን አስተባብረው አስነስተውት የነበረው ረብሻ ሊዛመት ሞክሮ ነበር፡፡

ይህን በመጠቀም በፒያሣና በመርካቶ የተካሄደው ዝርፊያና ሱቅ መስበር ሌላም በካሜራ ተቀርጾ ዛሬም ድረስ ማስረጃው ይገኛል፡፡ ሠላማዊ ትግል ማለት በኃይል የታጀበና የራሱን የጥፋት ቡድን ያደራጀ፤ ያስታጠቀ፤ ሰው የሚገድልና ዝርፊያ የሚያካሂድ፤ ንብረት የሚያወድም ነው ያለው ማነው? እናንተስ ከዚህ የምታተርፉትና የምትጠቀሙት

ምንድነው? በዚህ መልኩስ እንዴት ድል አድርገን የፖለቲካ ሥልጣን ይዘን አገር እንመራለን ብላችሁ ታስባላችሁ?

ይኼ ድግሳችሁ አመጽ፣ ሁከት፣ ሥራ ማቆም አድማ፣ ረብሻ ወዘተ...እንዳሰባችሁት ሳይሳካ ቢቀር የፖለቲካ መንበሩን መያዝ ባትችሉስ ቀጣዩ ጉዳይ ምን የሚሆን ይመስላችኋል? ኔቶ ሠራዊትና ኃይል ይልክላችሁ ይሆን ወይንስ የአየርና የመርከብ እርዳታ ለሰማያዊ ፓርቲና ለግንቦት ሰባት፣ ለአንድነትና ለመኢአድ ወይንም ለአክራሪው ፅንፈኛ ያሳልፍላችሁ ይሆን?

ይህ ሁሉ እኛ ሥልጣን ካልያዝን አገርም ሕዝብም ይውደም፣ በደም ይራጭ የሚለው ከከፋ የሥልጣን ጥማትና አራራ የመነጨ የደኸየው አስተሳሰባችሁ የትም ሳይደርስ ሩቅ ሳይጓዝ በዓይናችሁ ፊት መክኖ ይቀራል፡፡ በምታመጡት ጥፋትና ውድመት የተነሳ ሕዝቡ ተቃዋሚ የሚባለውን ነገርና አስተሳሰብ እስከ ወዲያኛው አንይ፣ አንስማ፣ የሚል አስተሳሰብ ሊይዝ ይችላል፡፡ ይህም ሠላማዊ ትግልን የሚከተሉ ተቃዋሚዎችን ለአገር የሚጠቅም ገንቢ አስተዋጽኦ እንዳይነሳ አድርጋችሁ ቀበራችሁት ገደላችሁት ማለት ነው፡፡

መቼም አንዴ በቀለም አብዮት ልክፍት እና ፍቅር ነዳችሁ ጠፋችኋልና፣ ተኝታችሁም ተነስታችሁም የምታስቡት በኒዮ ሊበራል ኃይሎች ከጀርባ እየተደገፋችሁ አይዟችሁ በርቱ ለሥልጣን እናበቃችኋለን ተብላችኋልና ጥፋት እንዲከሰት ከማድረግ ወደ ኋላ እንደማትሉ ብዙ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ያልተረዳችሁት ትልቁ ነጥብ የኢትዮጵያ መሪና አስተዳዳሪ ሕዝብ እንጂ ኒዮ ሊበራል ኃይሎች ወይንም የእነሱ ሎሌና ጋሻ ጃግሬዎች አይደሉም፡፡

እያስፔድ እንደገለፅከው በ1997 ዓ.ም ቅንጅት ለምርጫው የቀለም አብዮት በኢትዮጵያ ለማካሄድ ሰባ ሚሊዮን ብር አወጣ፡፡ ይህንንም ገንዘብ ደጋፊና አባላት ሙሉ በሙሉ አዋጡ የሚል ውሸት ውስጥ አትገባም፡፡

ሰባ ሚሊዮን ብር የተገኘው በኢትዮጵያ የኒዮ ሊበራል ኃይሎችን የፖለቲካና የኢኮኖሚ መስመርን የሚደግፍ፣ የአገሪቱን ሐብት ሙሉ በሙሉ ለምዕራባዊያን ከበርቴዎችና ኩባንያዎቻቸው አሳልፎ የሚሰጥና የሚያስበዘብዝ አደግዳጊና አሽከር መንግሥት ለማቋቋም ገንዘቡ በእነ ፕሮፌሰር መሥፍን፣ በዶክተር ብርሀኑ ነጋ አማካይነት ከአፍቃሪው ኒዮ ሊበራል ዓለም አቀፍ ከበርቴ ጆርጅ ሶሮስ ካዝና የተገኘ መሆኑን እናንተም አትክዱትም፡፡ ዛሬም እየሰጣችሁ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ከአባላት መዋጮ ውጭ ሌላ የገንዘብ ምንጭ የላቸውም የሚለው አባባል ውኃ እንደማያነሳ የቅንጅቱ ሰባ ሚሊዮን ብር ከውጭ የተገኘ የዓላማ ማሣኪያ፣ የአመፅና ሁከት ማነሳሻ፣ በተግባር ለሚሳተፉ የሚውል ክፍያ መሆኑ ይታወቃል፡፡

የግሉ ፕሬስም በ1997 ዓ.ም በዚሁ ገንዘብ ተገዝቶ ነው የተሰለፈው፡፡ …በበላበት ይጮኃል እንዲሉ፡፡ ባህር ማዶ ሆነው ለኢትዮጵያ መልዕክት የሚያስተላልፉት የፅንፈኛው ራዲዮ ጣቢያዎች በተለያየ ሞገድ እየተጠቀሙ ሕዝቡ ለአመጽ እንዲነሳ ዘረኛ መልዕክት እያስተላለፉ ሲቀሰቅሱ የነበረውም በዚሁ ገንዘብ ነበር፡፡

አየሁ እያስፔድ፣ ቅንጅቱ ሰባ ሚሊዮን ብር የቀለም አብዮት እንዲያካሂድ ተሰጥቶት፣ በሕዝብ አመፅና ሁካታ በኃይል መንግሥትን እንዲያስወግድ መፈንቅለ መንግሥት እንዲያካሂድ ተመድቦለት እንኳ ሊሳካለት አልቻለም፡፡ አሸነፍኩ ያለውን አዲስ አበባን እንኳን አስተዳድር ተብሎ ሲለቀቅለት አላስተዳድርም እሺ ፖርላማ ባገኛችሁት ድምጽ መሠረት ገብታችሁ ተሳተፉ፣ አንሳተፍም፣ ፓርላማም አንገባም ብለው አረፉ፡፡ የለም ያሸነፍነው መላውን ኢትዮጵያ ነው፣ ሁሉንም መያዝ አለብን አሉ፡፡ ገዥው ፖርቲ ያሸነፈባቸውን ቦታዎች ሁሉ ካዱ፡፡

እነሱ ልክ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ሰባ ሚሊዮን ብር ከወጭ ኃይሎች የተመደበላቸው ሙሉ በሙሉ የፖለቲካ ወንበሩን እንዲይዙና ከቅንጅት ጀርባ ኒዮ ሊበራል ኃይሉ ኢትዮጵያን እንዲመራ ነበር፡፡ አዲስ አበባ ላይ ማሸነፍ ማለት (በብዙ ምክንያት ከቀድሞውም ሥርዓት ጋር በተያያዘ ተቃዋሚው ይበዛልና) ድፍን ኢትዮጵያ ያለውን መራጭ ሕዝብ ድምፅ ጠቅልዬ ልወስድ አያስብልም ነበር፡፡

ቅንጅቱ በእውነት ለአገርና ለሕዝብ አሳቢና ተቆርቋሪ ቢሆን ኑሮ አዲስ አበባንም ተረክቦ ፖርላማም ገብቶ እየሰራ የሕዝብ ተወካይነቱን ማሳየት ይችል ነበር፡፡ ይህ ማንቂያ ደወል የጠቀመው ገዢው ፓርቲ ከዚያ ወዲህ ታላላቅ ሕዝባዊ ሥራዎችን መከወኑን ሕዝቡም ዓለምም መስክሮለታል፡፡

እንግዲህ ቅንጅት ከውጭ ኃይሎች ምርጫውን እንዲያሸንፍ የተሰጠው ገንዘብ ለፕሮፓጋንዳ ሥራ፣ ለጋዜጦች ለግሉ ፕሬስ፣ ለመሪዎቹ ውሎ አበልና መዝናኛ በሚል

በግለሰቦች ተመዝብሮ፤ የላቀ ሙስና የተፈፀመበትና በኋላም እርስ በእርስ እንዲወነጃጀሉና እንዲባሉ ያደረጋቸው ገንዘብ ነው፡፡

እዚህ ያሉትም አመራሮቹ አሜሪካና አውሮፓ ያሉትም ዘርፈው በግልና በቤተሰቦቻቸው አካውንቶች አስገብተዋል በሚል አሜሪካን ፍርድ ቤት የተከሰሱበትንም የትናንት ታሪክ በመገናኛ ብዙኃን ወጥቶ አይተናል፡፡ አዲትም ተጠያቂነትም የሌለበት ገንዘብ በመሆኑ ተቀራምተውታል፡፡

እንግዲህ ለሕዝብ እናስባለን፤ ለአገር እንቆረቆራለን፤ ኢትዮጵያ አገሬ ባንዲራዬ ሞቼ ልቀበርልሽ እያሉ የሚያደነቁሩን የእኛ ተቃዋሚዎች እነዚህ ናቸው፡፡ በአገር አመራር ላይ ደግሞ ቢቀመጡ ይኸው ኃላፊነት የጎደለው ግለኝነት የተጠናወታቸው በዝርፊያ በመክበር በሚያምነው ስብዕናቸው ጭራሹን አገሪቷን ግጠው እንደሚያራቁቷት ለአፍታ መጠራጠር አይቻልም፡፡

የራሳቸውን ጉድፍና ገመና ሁሌም ለማየትና ለመፈተሽ፤ ከውድቀትና ከስህተታቸውም ለመማርና የተሻለ ሆኖ ለመገኘት ጭርሱንም የማይሞክሩ፤ ውኃ ቅዳ ውኃ መልስ የመሆናቸው እውነታ ተስፋችንን ያሟጠዋል፡፡ ዛሬም የ1997ቱ ቅንጅት ነው አንድነት፣ መድረክ፣ ሰማያዊ ፓርቲ፣ መኢአድ…ግንቦት ሰባት ምናምን ወዘተ ሆኖ ተሸራርፎና ተበታትኖ፤ የጋራ ራዕይም አጥቶ መቼም ሊኖረው አይችልምና ደግሞም አገሪቷንና የፈረደበትን ሕዝብ ላምሰው እያለ ያለው፡፡ በማንም መቀለድም ሆነ ማላገጥ አይችሉም፡፡

አሁን ደግሞ ስንት መቶ ሚሊዮን ዶላር ተቀብለው ሊያባሉን፣ ሊያናቁሩንና ሊሸጡን እንደተነሱ እነሱው ያውቃሉ፡፡ ክፍያው ቀድሞ ለመሰራጨቱ ምስክሮቹ የግሉ ፕሬስ መፅሄቶች ቀደም ብለው ሰፊ የማጥላላትና የፕሮፓጋንዳ ሥራ ሲከውኑ፤ መንግሥትን ከሕዝብ ለመነጠል ሲውተረተሩ፤ የመሪዎችን ስብዕና በመወንጀልና በማጣጣል የአገሪቱን ልማትና እድገት በማጣጣል ወዘተ…ሲሰሩ የከረሙት በቂ ምስክር ነው፡፡

እነ ሰማያዊ ፓርቲም በአዲስ ሥያሜ የተደራጁት፤ ነባሮቹም የሚደገፉት በዚሁ የውጭ ኃይሎች ገንዘብ ነው፡፡ ይህም ሆኖ እንደማያዋጣቸው ሲገባቸው ገና ከአሁኑ እንበጥብጥ፤ እንረብሽ እንጂ ምርጫ ውድድር ውስጥ ብንገባ ስለምንሸነፍ ውድድሩ ውስጥ አንገባም ማለት ይሻላል የሚል አቋም የያዙትም ለዚሁ ነው፡፡

በምርጫው ከሚሳተፉት ፓርቲዎች አንዳንዶቹ የመመረጥ እድል ይኖራቸዋል፡፡ ለሕዝቡ በተከናወኑት ተጨባጭ አገራዊ የልማት ሥራዎች፣ በተመዘገቡ ፈጣን እድገቶች፣ ይህን ያስገኘው ገዢው ፓርቲ በሕዝቡ ከፍተኛ ድምፅ እንደሚመረጥ ማንም አይጠራጠርም፡፡ ስህተቶቹን እያረመ፣ እያስተካከለ፣ ሕዝብን እያዳመጠና እያሳተፈ የበለጠ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥኬት እንደሚያመጣ ሕዝቡም ያምናል፡፡

ይህን የሚያውቀው ተቃዋሚ ከአሁኑ ከምርጫው አንድ ዓመት በፊት አልወዳደርም ብሎ ሲያውጅ ምዕራባውያኑ በመገረም ይስቃሉ፡፡ ይህን የሚለው ተቃዋሚው በሕዝቡ ምርጫ በዝረራ እንደሚሸነፍ ስለሚያውቅ ነው፡፡

እንኳን አንድን ታላቅ አገር፣ ታላቅ ሕዝብ ለመምራት ይቅርና ተቃዋሚው ገና እርስ በእርስ ከመባላት ያልወጣም ስለሆነ ነው፡፡ ይህን ድክመቱን ስለሚያውቅ ምርጫ ገብቶ ከመወዳደር፣ ተሰልፎ በሽንፈት ከመውጣት፣ ውድድሩ ውስጥ አልሳተፍም እያለ ፕሮፓጋንዳ ከአሁኑ የሚነዛው ያለውን አቅም ስለሚያውቅ ነው፡፡

አገር በጩኸት፣ በሠላማዊ ሰልፍ፣ በግርግር፣ በስም ማጥፋት፣ በስሜታዊነት አትመራም፡፡ ስክነት፣ ብስለት፣ እርጋታና አስተዋይነትን ትጠይቃለች፡፡ እመረጣለሁ ያለ ሁሉም መሪ አይሆንም፡፡ አገርንና ትውልድን የሚለውጡና ለቀጣዩም ታላቅነት የሚያበቁ ተቋማትን መገንባት፣ ልማት ማካሄድ፣ እድገት ያመጣል፣ በአገርና በሕዝብ ስም ፖለቲካን፣ ንግድን ማትረፊያ አድርገው በሚያድሩ ግለሰቦች የሚመሩ ፓርቲዎችን ማቋቋምና መጮህ ውርደትም፣ ውድቀትም ነው፡፡

እነዚህ ስመ ብዙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ገዥው ፓርቲ ሥልጣን ላይ እያለ ብዙ ጊዜ ሲፈርሱና ሲበታተኑ አንድ የነበሩት አራት…አምስት ከዚያም በላይ ሲሆኑ ዛሬም እዚያው ናቸው፡፡ ነገም በተግባር እናየዋለን፡፡ በዚህ መልኩ የልጅ ጨዋታ አድርገውት በአገርና በሕዝብ ላይ እንዲቀልዱ የሚፈቅድ እንደ ኢያስፔድም የሚያብድ የለም፡፡

መስከረም ላይ ትግሉ ቢጀመር ጥሩ ነው ሲል ኢያስፔድ የገለፀውም ሀሳብ በፋክት መፅሔት የሕዳሴው ለውጥ ጽሁፍ ተመስገን ደሣለኝ ያነሳው ሀሳብና የመረጠው ወር ነው፡፡ የእናንተን የሠላማዊ ትግል ሥልትና ዘዴ ተቀብሎ የሚወጣና የሚተገብር ሕዝብ የለም፡፡ ጥቂቶች ብጤዎቻችሁን ግን አታጡም፡፡

ኢ.ያስፔድ ስለጆሴፍ ስታሊንም ሆነ ስለ ሰሜን ኮርያ ብዙ የምታውቀው ጉዳይ እንደሌለ ጽሑፍህ ይናገራል፡፡ እውቀቱ ቢኖርህ ያልከውን ከማለት ትቆጠብ ነበር፡፡ አንተ የኒዮ ሊበራል ኃይሎች ኩትኩትና አምላኪ ነህ፡፡ የጠቀስካቸው ደግሞ ፍጹም ፀረ ኒዮ ሊበራል ክፍሎች ናቸው፡፡ ለሁሉም ከገባህበት የቅዠት ሰመመን ውጣና በእርጋታ አስብ፤ ወደ እውነቱ ተመለስ፡፡ የጎነጎናችሁት የአመጽና የረብሻ ገመድ ይበጣጠሳል፡፡ ሴራችሁም ዓይናችሁ እያየ ይፈራርሳል፡፡ እንዲያም ሆኖ በምርጫው መሳተፍ ያለባቸውም ይሣተፋሉ፡፡